የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# የድጋሚ ምርጫ አፈፃፀም መመሪያ
# ቁጥር 15/2013 ዓ.ም

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 1. <u>አውጪው ባለስልጣን</u>**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 20፣ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (1) እና ንዑስ አንቀጽ (4) እና የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ (3) ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

**አንቀጽ 2. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ መመሪያ ***“የድጋሚ ምርጫ መመሪያ ቁጥር 15/2013”*** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀጽ 3. <u>ትርጓሜ</u>**

1. **“አዋጅ”** ማለት የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁ. 1162/2012።
2. **“ቦርድ”** ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው።
3. **“ድጋሚ ምርጫ”** ማለት ቦርዱ የምርጫ ውጤት እንዲሰረዝ ሲወስን፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቀረበለት አቤቱታ ላይ ተመስርቶ ምርጫ እንዲደገም ሲወስን ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን ለመለየት የሚካሄድ ምርጫ ነው።

4. **"ዋና ምርጫ"** ማለት የድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ በተወሰነበት የምርጫ ክልል ወይም ጣቢያ ላይ የተካሄደው የምርጫ ሂደት ነው፡፡
5. **"የምርጫ ሂደት"** ማለት የመራጮ ምዝገባ፣ የዕጩ ምዝገባ፣ የምረጡኝ ቅስቀሳ፣ የመገናኛ ብዙኃን ተደራሽነት፣ የድምፅ አሰጣጥ፣ የድምፅ ቆጠራ፣ ጊዜያዊ ውጤት አደማመር፣ የቅሬታ አፈታት ሥርዓት እና የመጨረሻ የምርጫ ውጤት ማሳወቅን የሚያካትት ነው፡፡
6. የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በአዋጁ ላይ የተሰጡ ለዚህ መመሪያ አግባብነት ያላቸው ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

### አንቀጽ 4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

በዚህ መመሪያ መሰረት የድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ በተወሰነባቸው ምርጫ ክልል ወይም ምርጫ ጣቢያ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 5. <u>የፆታ አገላለፅ</u>

በዚህ መመሪያ በአንዱ ፆታ የተደነገገው አነጋገር የሌላኛውን ፆታም ያካትታል፡፡

### አንቀጽ 6. <u>ዓላማ</u>

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የድጋሚ ምርጫ አፈጻጸም ለመወሰን እና፣
2. ድጋሚ ምርጫ የሚደረግበትን አግባብ እና ቦርዱ እና በየደረጃው የሚገኙ የሚመለከታቸው የምርጫ አስፈጻሚዎች ያለባቸውን ሀላፊነት ግልፅ ለማድረግ ነው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## <u>የድጋሚ ምርጫ ተፈፃሚ የሚሆንበት ሁኔታ እና አሠራር</u>

### አንቀጽ 7. <u>የድጋሚ ምርጫ ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምርጫ ሂደቱን በሚመለከት የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ የድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ሲወስን ቦርዱ ይህንን ውሳኔ ተቀብሎ ማስፈጸም አለበት፡፡

2. ቦርዱ በምርጫ ሂደት የምርጫ ውጤቱን ሊያዛንፍ የሚችል የህግ ጥሰት በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የምርጫ ክልሎች ተፈፅሟል በማለት ሲያምን ጥሰቱ በተፈፀመባቸው ምርጫ ክልሎች ወይም ምርጫ ጣቢያዎች ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ሊወስን ይችላል።
3. ቦርዱ የተፈፀመው ስህተት የምርጫ ውጤቱን የሚያዛንፍ ነው ብሎ ለመወሰን የሚከተሉትን ሁኔታዎችች ከግምት ውስጥ ያስገባል፡-

ሀ) የምርጫውን ውጤት ሊቀይር የሚችል ቁጥር ያለው መራጭ ድምጽ እንዳይሰጥ የተከለከለ እንደሆነ፤

ለ) የምርጫውን ውጤት ሊቀይር የሚችል ቁጥር ያለው መራጭ ተገዶ ለአንድ ወገን ድምጽ እንዲሰጥ የተደረገ እንደሆነ፤

ሐ) የምርጫውን ውጤት ሊቀይር የሚችል ቁጥር ያለው መራጭ ላይ ሆነ ተብሎ በተደረገ ህጋዊ ያልሆነ ተግባር ምክንያት የአንድ ፓርቲ ወይም እጩ ደጋፊዎች የፈለጉትን እንዳይመርጡ የተደረገ እንደሆነ፤

መ) የምርጫውን ውጤት ሊቀይር የሚችል ቁጥር ያለው ድምጽ መስጫ ወረቀት የጠፋ፣ የተቀደደ፣ የተበላሸ በመሆኑ ለመቁጠር የማይቻል ድምፅ እንዲሆን ከተደረገ፤

ሠ) የተሰጠው ድምጽ ለመስጠት ከተመዘገበ መራጭ በላይ በልጦ የተገኘ እንደሆነ እና ሁኔታው ድጋሚ ቆጠራ በማድረግ ካልተስተካከለ፤

ረ) በምርጫ ክልሉ በሚገኙ በአብዛኞቹ የምርጫ ጣቢያዎች ላይ  መራጮችን ወይም ተወዳዳሪዎችን ወይም ወኪሎቻቸውን ወይም የቦርዱ አስፈፃሚዎች ላይ ፍርሀት እና መሸማቀቅ የሚፈጥር የሀይል ተግባር ስለመፈፀሙ በማስረጃ ከተረጋገጠ፤

ሰ) ከላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች ውጪ የተወሰኑ ምርጫ ጣቢያዎች ወይም ምርጫ ክልሎች ላይ የተረጋገጠ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ በመከሰቱ ምክንያት የተሰጠውን ድምፅ መቁጠር ወይም ውጤቱን ማወቅ ካልተቻለ እና አሸናፊውን መለየት ያልተቻለ እንደሆነ ቦርዱ ድጋሚ ምርጫ የሚካሄድበትን ሁኔታ ሊወስን ይችላል።

4. ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምጽ ካገኙ እና ይህም በድጋሚ ቆጠራ በመረጋገጡ ምክንያት አሸናፊውን መለየት ካልተቻለ ቦርዱ እኩል ድምጽ ባገኙት ተወዳዳሪዎች መካከል

ብቻ ድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል። እንደዚህ ባሉ ሁኔታዎች ከተወዳዳሪዎቹ አንዱ እራሱን ከምርጫው ካገለለ ድጋሚ ምርጫ አስፈላጊ አይሆንም።

5. በክልል ም/ቤት ወይም በአከባቢ ምርጫ ወቅት እኩል ድምጽ ያመጡት እጩዎች እና ለውድድር የቀረቡት ወንበሮች ብዛት እኩል ከሆነ ድጋሚ ምርጫ ማድረግ አያስፈልግም።

## **አንቀጽ 8. <u>የውሳኔው ይዘት</u>**

1. ቦርዱ የድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ውሳኔ ላይ የደረሰ እንደሆነ፡-

   ሀ) ውሳኔው የተሰጠበት ቀን፣

   ለ) ድጋሚ ምርጫ የሚደረግበት የምርጫ ክልል ወይም የምርጫ ጣቢያ፣

   ሐ) ድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ ያበቃው ምክንያት ከነማብራሪያው እና፣

   መ) የምርጫው አይነት እና ድጋሚ ምርጫው የሚደረግበትን ጊዜ ገልፆ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እና ግልጽ በሆነ መንገድ ምርጫው ከታቀደበት ከአስር ቀናት በፊት ማሳወቅ እና ይህንኑ ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ በተወሰነበት የምርጫ ክልል ወይም የምርጫ ጣቢያ ላይ መለጠፍ አለበት።

2. የድጋሚ ምርጫ ውሳኔው የተላለፈው በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሆነ ቦርዱ፡-

   ሀ) የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ያስተላለፈበትን ውሳኔ መዝገብ ቁጥር፣

   ለ) ውሳኔው የተሰጠበት ቀን፣

   ሐ) ድጋሚ ምርጫ የሚደረግበት የምርጫ ክልል ወይም የምርጫ ጣቢያ እና፣

   መ) የምርጫው አይነት እና ድጋሚ ምርጫው የሚደረግበትን ጊዜ ገልፆ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እና ግልጽ በሆነ መንገድ ድጋሚ ምርጫው ከታቀደበት ከአስር ቀናት በፊት ማሳወቅ እና ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ በተወሰነበት የምርጫ ክልሉ ወይም የምርጫ ጣቢያ መለጠፍ አለበት።

3. የድጋሚ ምርጫ የሚደረገው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት ከሆነ ቦርዱ፡-

   ሀ) እኩል ድምፅ ያገኙት ተወዳዳሪዎችን ሙሉ ስም፣

   ለ) የእጩ መለያ ምልክቶቻቸው፣

ሐ) የሚወዳደሩት በግል ወይም በፖለቲካ ድርጅት እጩነት መሆኑን በመለየት የፖለቲካ ድርጅት እጩ የሆነው ላይ የሚወክለው የፖለቲካ ድርጅት ስም፤ የግል እጩ የሆነው ላይ ደግሞ የግል እጩ መሆኑን በመግለጽ፣

መ) ውሳኔው የተሰጠበት ቀን እና፣

ሠ) ድጋሚ ምርጫው የሚደረግበትን ጊዜ ገልፆ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እና ግልጽ በሆነ መንገድ ድጋሚ ምርጫው ከታቀደበት ቀን ከአስር ቀናት በፊት ማሳወቅ እና ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ በተወሰነበት የምርጫ ክልል ወይም የምርጫ ጣቢያ መለጠፍ አለበት።

## አንቀጽ 9. <u>ድጋሚ ምርጫ ስለሚደረግበት የምርጫ ጣቢያ</u>

1. የድጋሚ ምርጫ የሚካሄድበት የምርጫ ጣቢያ ዋና ምርጫ የተከናወነበት የምርጫ ጣቢያ ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ላይ የተደነገገው ቢኖርም ቦርዱ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን የድጋሚ ምርጫ የሚደረግበት የምርጫ ጣቢያ ቦታ እንዲቀየር ሊወስን ይችላል።
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (2) መሰረት የምርጫ ጣቢያው አድራሻ የተቀየረ እንደሆነ ቦርዱ ይህንን የቦታ ለውጥ አስመልክቶ ከድጋሚ ምርጫ ቀን ቢያንስ አምስት ቀናት በፊት ማሳወቅ አለበት።

## አንቀጽ 10. <u>የመራጮች ምዝገባ</u>

ቦርዱ ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ ውሳኔ የሰጠ እንደሆነ ሌላ አዲስ የመራጮች ምዝገባ ሳያስፈልግ ድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ በተወሰነበት ምርጫ ክልል ወይም በዚሁ ምርጫ ክልል ውስጥ ችግሩ በተከሰተባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ተመዝግበው በነበሩ መራጮች እንደገና ይካሄዳል። በመሆኑም መራጮች ማንነታቸውን የሚያሳይ መታወቂያ እያሳዩ በመራጮች መዝገብ ላይ መመዝገባቸው ተረጋግጦ ድምፅ እንዲሰጡ ይደረጋል።በምስክር ተመዝግበው የነበሩ መራጮችም በድምፅ አሰጣጥ እና ቆጠራ መመሪያ ላይ በተቀመጠው መሰረት የሚመርጡ ይሆናል።

## አንቀጽ 11. <u>ለድጋሚ ምርጫ መቅረብ ስለሚችሉ እጩዎች</u>

1. ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ የተወሰነው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ድጋሚ ምርጫው አዲስ የእጩዎች ምዝገባ ሳያስፈልግ ቀድሞ በተመዘገቡ እጩዎች መካከል ይደረጋል።

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም እኩል ድምጽ ያመጣ እጩ ቢሞት ፓርቲው ሌላ እጩ መተካት ይችላል፡፡
3. ለድጋሚ ምርጫ የሚወዳደሩ እጩዎች የሚጠቀሙበት መወዳደሪያ መለያ ምልክት ለዋና ምርጫ የተጠቀሙበት መለያ ምልክት ይሆናል፡፡
4. የድጋሚ ምርጫ የሚደረገው ሁለት ወይም ከሁለት በላይ እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው አሸናፊውን ለመለየት ካልተቻለ ለድጋሚ ምርጫው እንደ እጩ ተወዳዳሪነት መቅረብ የሚችሉት እኩል ድምጽ ያገኙት ተወዳዳሪዎች ብቻ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 12. <u>የድምጽ መስጫ ወረቀት</u>**

1. ቦርዱ ለድጋሚ ምርጫ፣ ለዋናው ምርጫ የታተመውን የድምጽ መስጫ ወረቀት ወይንም አዲስ የድምፅ መስጫ ወረቀት አሳትሞ ሊጠቀም ይችላል፡፡
2. የድጋሚ ምርጫ የሚደረገው ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምጽ በማግኘታቸው ምክንያት ከሆነ ድምጽ መስጫ ወረቀቱ የሚዘጋጅበትን አግባብ ቦርዱ ይወስናል፡፡
3. የድጋሚ ምርጫ የሚደረገው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ከሆነ እና ድምጽ መስጫ ወረቀቱ የያዘው የድጋሚ ምርጫ እጩዎችን ብቻ ከሆነ የእጩዎቹ ፎቶግራፍና መለያ ምልክት የአቀማመጥ ቅደም ተከተላቸው በዋና ምርጫ ላይ በነበረው ቅደም ተከተልን መሰረት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 13. <u>የድምፅ አሰጣጥ እና ቆጠራ</u>**

1. የድጋሚ ምርጫ ድምጽ አሰጣጥ እና ቆጠራ ሂደት በአዋጁ መሰረት እና በድምፅ አሰጣጥ፣ የድምፅ ቆጠራ እና የውጤት አገላለፅ መመሪያ መሠረት የዋናው ምርጫ ድምጽ አሰጣጥ ሂደት የተከተለ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የድጋሚ ምርጫ ላይ ለመጀመሪያ ምርጫ በሚደረገው መልኩ አንድ መራጭ ድምጽ እንደሰጠ የሚገልጽ እና ከአንድ ጊዜ በላይ ድምጽ እንዳይሰጥ ለመከላከል የሚረዳ በጉልህ በሚታይ መልኩ ለዋና ምርጫ ከተቀባው ጣት የተለየ ጣት ላይ ቀለም መቀባት አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ድጋሚ ምርጫ ላይ ድምፅ የሰጠ መራጭ ድጋሚ ምርጫ ላይ መሳተፉን የሚገልፅ ፊርማ ቦርዱ በሚወስነው አግባብ እንዲፈርም ይደረጋል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ላይ የተደነገገው ቢኖርም ቦርዱ ሌላ አሰራር እንዲከተል የሚያስገድደው ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር የድጋሚ ምርጫ የድምፅ አሰጣጥ እና ቆጠራ ዋናውን ምርጫ ለመታዘብ ፍቃድ የተሰጣቸው ታዛቢዎች፣ ጋዜጠኞች እና በድጋሚ የተወዳደሩ እጩ ተወዳዳሪዎች ወኪሎች በተገኙበት በምርጫ ጣቢያው ይካሄዳል።

## አንቀጽ 14. <u>የድጋሚ ምርጫ ውጤት ይፋ ስለማድረግ</u>

1. ቦርዱ ድጋሚ ምርጫ ውጤትን ይፋ የሚያደርገው እንደአግባብነቱ በአዋጁ እና በድምፅ አሰጣጥ፣ የድምፅ ቆጠራ እና የውጤት አገላለፅ መመሪያ መሰረት  በምርጫ ጣቢያ እና በምርጫ ክልል በመከፋፈል መሆን አለበት። የድጋሚ ምርጫ ውጤት ይፋ የሚደረገው አዋጁ እና የድምፅ አሰጣጥ፣ የድምጽ ቆጠራ እና የውጤት አገላለጽ መመሪያ መሰረት  ለዋና ምርጫ ውጤት አገላለጽ ያስቀመጡትን አሰራር ተከተሎ ይሆናል።
2. ቦርዱ የድጋሚ ምርጫ ውጤት ይፋ ሲያደርግ በተጨማሪ፡-
   ሀ) የድጋሚ ምርጫ የተወሰነበትን ምክንያት፣
   ለ) ውሳኔውን የሰጠውን አካል፣
   ሐ) ውሳኔው የተሰጠበት ቀን እና፣
   መ) ድጋሚ ምርጫው የተደረገባቸው ጣቢያዎች እና የምርጫ ክልል ጠቅሶ መሆን አለበት።

## አንቀጽ 15. <u>የድጋሚ ምርጫ ሂደት ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ</u>

1. የድጋሚ ምርጫ ሂደት ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች አፈታት ሂደት እና ስነ ስርአት በምርጫ ሂደት በየደረጃው ስለሚኖር አቤቱታ አቀራረብ፣ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አደረጃጀት እና አሠራር መመሪያ መሠረት ይወሰናል።
2. የድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ የተሰጠው ውሳኔ በዋናው ምርጫ የነበሩ የምርጫ አስፈፃሚዎች ወይም የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴዎች እንዲቀየሩ የማድረግ ውጤት ሲኖረው ቦርዱ ይህን ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎችን ያከናውናል።

## ምዕራፍ ሶስት

## ኃላፊነቶች

### አንቀጽ 16. የቦርዱ ኃላፊነቶች

1. ቦርዱ ለምርጫ አስፈጻሚዎች የሚያዘጋጀው ስልጠና የድጋሚ ምርጫ አሰራር እና አፈፃፀምን ማካተት አለበት።
2. ቦርዱ የድጋሚ ምርጫ የሚካሄድ መሆኑን ባወቀ ጊዜ የድጋሚ ምርጫ ውሳኔ ከተሰጠበት ወይም እኩል ድምፅ በማግኘታው አሸናፊውን መለየት ካልተቻለ ድጋሚ ምርጫ እንደሚደረግ ይፋ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በተቻለ ፍጥነት ድጋሚ ምርጫውን ማካሄድ አለበት።
3. የድጋሚ ምርጫ እንደሚደረግ ሲታወቅ ቦርዱ ይህንን አስመልክቶ ለህብረተሰቡ እና ለመራጮች ተደራሽ በሆነ አኳኋን ዝርዝር ውሳኔውን እና ቀጣይ ሂደቱን ለማሳወቅ የሚያስችል የመራጮች ትምህርት መስጠት አለበት።
4. ቦርዱ የድጋሚ ምርጫ የሚደረግበትን የጊዜ ሰሌዳ እና አሰራር በዝርዝር ማሳወቅ አለበት።

### አንቀጽ 17. የእጩ ተወዳዳሪዎች ኃላፊነቶች

1. በድጋሚ ምርጫ ላይ የሚሳተፉ እጩዎች ወይም ወኪሎች ድጋሚ ምርጫ እንደሚደረግ ግልጽ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ድጋሚ ምርጫ ከሚደረግበት ከምርጫ ክልሉ እና ምርጫ ጣቢያ የምርጫ አስፈፃሚዎች ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው።
2. በድጋሚ ምርጫ ላይ የሚሳተፉ እጩዎች ወይም ወኪሎች ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ የድጋሚ ምርጫ ውጤት ይፋ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ ለድጋሚ ምርጫ የምርጫ ቅስቀሳ ማድረግ አይችሉም።
3. በድጋሚ ምርጫ ላይ የሚሳተፉ እጩዎች ወይም ወኪሎች የፖለቲካ ድርጅት አባላት እና ደጋፊዎች የምርጫ ቅስቀሳ፣ የምርጫውን ሂደት የሚያደናቅፍ ማናቸውም ተግባር እና በማንኛውም መልኩ የሚደረግ የድጋፍ ማሳያ እንቅስቃሴ ከማድረግ እንዲቆጠቡ ማስገንዘብ አለባቸው።
4. ድጋሚ ምርጫውን ለመታዘብ ፍላጎት ያላቸው በዋናው ምርጫ ላይ ለመታዘብ ፈቃድ የተሰጣቸው የድጋሚ ምርጫ ተሳታፊ የእጩ ወኪሎች ፍላጎታቸውን ለቦርዱ እና ድጋሚ ምርጫ ለሚካሄድበት ምርጫ ክልል ማሳወቅ አለባቸው። ቦርዱ በማንኛውም ጊዜ በምርጫ ጣቢያው የሚገኙትን ፈቃድ

የተሰጣቸውን ወኪሎች ቁጥር መገደብ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ፍትሐዊነቱን በጠበቀ መልኩ ተራ በተራ በምርጫ ጣቢያው የሚገኙበትን አሰራር ሊዘረጋ ይችላል፡፡ ይህ ከሆነ ፍትሐዊነቱን የጠበቀ ተራ በተራ የሚገኙበት አሰራር በምርጫ ጣቢያው የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ሊገመገም ይገባል፡፡

**አንቀጽ 18.** **<u>የታዛቢዎች እና ጋዜጠኞች ኃላፊነቶች</u>**

1. ቦርዱ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ፍቃዳቸው የተሰረዘባቸው እስካልሆኑ ድረስ፤ ለዋናው ምርጫ ፍቃድ የተሰጣቸው ታዛቢዎች እና ጋዜጠኞች ሌላ ተጨማሪ ፍቃድ ሳያስፈልጋቸው ድጋሚ ምርጫውን የመታዘብ ወይም የመዘገብ መብት አላቸው፡፡
2. በድጋሜ ምርጫው የሚሳተፉ ታዛቢዎች፣ የሚዘግቡ ጋዜጠኞች እና የመገናኛ ብዙሃን የምርጫ ጣቢያዎችን፣ የምርጫ ክልሎችን እና ቦርዱን አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች መሰረት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡
3. ድጋሚ ምርጫውን ለመታዘብ ፍላጎት ያላቸው ለዋናው ምርጫ ፍቃድ የተሰጣቸው ታዛቢዎች እና ጋዜጠኞች ፍላጎታቸውን ለቦርዱ እና ድጋሚ ምርጫ ለሚካሄድበት ክልል እና ምርጫ ጣቢያ ማሳወቅ አለባቸው፡፡ ቦርዱ በምርጫ ወቅት የኮቪድ-19 ስርጭት ለመቀነስ ባወጣው መመሪያ መሰረት በምርጫ ጣቢያው ለመገኘት የሚያስችል ፍትሐዊነቱን የጠበቀ የተራ አሰራር በምርጫ ጣቢያው ይተገበራል፤ አፈፃፀሙም በአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ሊገመገም ይገባል፡፡
4. ድጋሚ ምርጫ ላይ በመገኘት የሚታዘቡ ታዛቢዎች የሃገር ውስጥ እና ውጭ ታዛቢዎችን ፍቃድ አሰጣጥ፣ አሰራር እና ስነ-ምግባርን በሚደነግጉ መመሪያዎች መሰረት ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡

## ምዕራፍ አራት

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**አንቀጽ 19.** **<u>ስለመተባበር</u>**

ማናቸውም የፌዴራልም ሆነ የክልል የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የፖለቲካ ድርጅት፣ ቡድን፣ የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ ይህንን መመሪያ በሥራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 20. <u>የተሻሩ ደንቦች እና አሠራሮች</u>**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም።

**አንቀጽ 21. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ በቦርዱ ከፀደቀበት ከሰኔ 20 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ብርቱካን ሚደቅሳ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ